

**መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.**

**ለ**

**ከሁሉ አስቀድመን ለመላው የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ካህናትና ምእናን መንፈሳዊ ሰላምታችንን ከአክብሮት ጋራ እናቀርባለን።**

**በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን!**

**በሁላችንም ዘንድ በግልጽ እንደሚታወቀው በሀገራችን በኢትዮጵያ በሚገኘው የእናት ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስና በዚህ በአሜሪካ ራሱን «ሲኖዶስ» ብሎ ሠይሞ በሚንቀሳቀሰው ቡድን መካከል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተነሣው ሁከት ከሁለቱም በኩል የመወጋገዝ ውሳኔ መተላለፉ ይታወሳል።**

**ከቀደምት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ በሆነችው ጥንታዊት ፣ ሐዋርያዊትና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ይህን የመሰለ ለኅሊና የሚከብድ ኢቀኖናዊ ድርጊት መከሠቱ እውነተኞቹን የቤተ ክርስቲያኒቱን ተከታዮች ካህናትንና ምእመናንን ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያኒቱን በጥንታዊነትዋና በቅድስና ታሪክዋ አውቀውና አክብረው የሚመለከትዋትን ሁሉ አሳዝኖአል። በእርግጥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ህልውና በበጎ ዐይን ለማይመለከቱ ወገኖችና ለነሱም በውስጥ መሳሪያነት ታጥቀው ለተነሡት ለምድ ለባሾች እንደ ጊዜያዊ ድል ሊታሰብ ይችል ይሆናል።**

**ይህን የታሪክ ወለምታ ዐይቶና ሰምቶ በዝምታና በልባዊ ሀዘን ማለፍ ለተከታታይ ጥፋቶች ምናልባትም ከፊተኛው ለሚከፉ የድፍረት ሥራዎች በር ከፍቶ እንደመተው ፣ ከዚህም በላይ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለክፉ ጊዜ የሚደርሱ የቁርጥ ቀን ልጆች የሌሉአት የወላድ መካን አድርጎ የሚያስቆጥር የኅሊና ጸጸት ነው።**

**በመሆኑም በአሜሪካ በገለልተኛነት ከሚገኙ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት የመጡ ካህናት ከየካቲት ፴ እስከ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.** (March 9-10, 2007) **በዲሲ. ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ባደረጉት ውይይት በሀገር ውስጥ ያለው የእናት ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ**

ራሱን «ሲኖዶስ» ብሎ ኢቀኖናዊ ተግባር እየፈጸመ በሚገኘው ቡድን ላይ ያሳለፈውን የውግዘት ቃል በመደገፍ የጋራ አቅዋም መግለጫ አውጥቶአል።

የካህናቱ ጉባኤ በወቅቱ አሳሳቢ ጉዳይ ላይ ትኩረት በመስጠት አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ተገቢ ናቸው ብሎ ባመነባቸው ጉዳዮች ውሳኔ ቢያሳልፍም በቀጣይ ሂደቱ ፥

- ምእመናንን በአባልነት የሚያካትት

- እስከ አሁን በገለልተኝነት መርኆ የሚተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት ካህናትን በስፋት የሚያሳትፍ

- መመሪያ ደንብና ሕጋዊ አካልነት ያለው ማኅበር ሆኖ እንዲቀጥል ስምምነት ተደርጎአል።

ስለዚህ ከወጣው የጋራ አቅዋም መግለጫ በተጨማሪ

- ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ተደራጅቶ ማስተማርን

- በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ገለልተኞች አብያተ ክርስቲያናት አንድነትና የኅብረት አገልግሎት ማመቻቸትን

- ሁል ጊዜ በድህነት ሲንገላታ የሚኖረውን ወገናችንን የኢትዮጵያን ሕዝብ በመሠረታዊ ፍላጎቶች በምግብ ፣ ልብስ ፣ መጠለያ ፣ በጤናና ትምህርት መስኮች የሚቻለውን እገዛ ለማድረግ የምግባረ ሠናይ ድርጅቶች አቋቁሞ መን ቀሳቀስን መሪ አላማዎቹ አድርጎ የተነሣው ማኅበር በሚገባ ተጠናክሮ በመቋቋሙ ላይ ብዙኃን ካህናትና ምእመናን እንዲካፈሉበት ለማድረግ ከሚያዝያ ፳፮ እስከ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. (May 4-5, 2007) በሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንዲደረግ በተወሰነው አጠቃላይ ስብሰባ ላይ ከቤተ ክርስቲያናችሁ ከካህናትና ምእመናን መካከል ተወካዮችን በመላክ የጉባኤው ተካፋይ እንድትሆኑልን አደራ ጭምር እናሳስባለን ፤ በዚህም አጋጣሚ ያለፈው ጉባኤያችን ያወጣውን የአቅዋም መግለጫ ሦስት ገጽ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ልዑል እግዚአብሔር የሀገራችንና የቤተ ክርስቲያናችንን ሰላምና አንድነት ይጠብቅልን!

ጸባቴ የማነ ብርሃን አሥራት
የጉባኤው ጊዜያዊ ሰብሳቢ